# እኔም እስክንድር ነኝ!

EthioLion

የጐንቻው!

የነፃነት ቀንዲል በፍትህ አማኝ፤
የሰላም ምርኮኛ ‘ሽብርን’ አምካኝ፤
ፍቅርን ሰባኪ የአንድነት  ወጋኝ፤
ለሕዝብ፤ለአገር ተሟጋች፤ታማኝ፤
ለሆዱ የማያድር በአሣር እሚዳኝ፤
አሳሪውን አስሮ በፍራት ፍጥኝ፤
ጓዳ እማይደብቁት፤ታላቅ ሰው ቋጥኝ፤
ዓለም እሚቃኘው ዓለም እሚያስቃኝ፤
የትውልድ በረከት፤ቅርጣን፤የሚያስገኝ፤
መንፈሱ፤ጽናቱ፤በእኔም የሚዋኝ፤
**ኢትዮጵያዊ አብራክ እኔ እስክንድር ነኝ።**

ስልጣን ዘርና ሃብት የማይደልለኝ፤
የአገር ክብር መብቴ፤ የበለጠብኝ፤
እትብት ከአሣር ምድር የተቆራኘኝ፤
የወያኔ ሽብር፤የአንገፈገፈኝ፤
የነፃነት ታጋይ፤ ለለውጥ እምቃኝ፤
እስሩን እጋራለሁ ቋጥሬ ስንኝ፤
ኖሬ ከምዋረድ፤ ባልኖር እምመኝ፤
የሰላም አርበኛ መስዋዕት፤ቢሻኝ፤
በእምነት በማተቤ፤ለእውነት የቆምኩኝ፤
የ’በላይ፤የአብዲሳ፤የግርማሜ’ ነኝ፤
ብዕሬን አሹዬ የአነጣጠርኩኝ፤
እስሩን እፈታለሁ፤ ቋጥሬ ስንኝ፤
ሸፍቼ አደባባይ የተዋጋሁኝ፤
ገመና ወያኔን ስላሳጣሁኝ፤
እኩዮች፤ግልምቢጥ፤‘ወያኔ’ ቢሉኝ፤
**ስሜ የሚያኮራ እኔ እስክንድር ነኝ።**

ሽብር አበሳችን ‘መስቀል’ እስኪዳኝ፤
በቃሊቲ ግዞት፤አንድ አይደለሁኝ፤
ጊዜ እያመቻቸሁ፤ በቋፍ እምገኝ፤
በምድረ ኢትዮጵያ፤ሰባ ሚሊዩን ነኝ፤
ወናውን ለቀረ፤ለአሳሪው ይብላኝ፤
እኔማ በአሳሬ ምን ተለይብኝ፤
ጀግናው ጐረቤቴ ‘አንዷለም’ አለኝ፤
‘ኦልባናም’፤ ‘ደበበ’ ‘ዘመን ሞላልኝ’፤
‘ርዕዮት ዓለሙ’፤ ‘ውብሸት ታዬኝ’፤
ምድራችን ስታርድ ተግሬ እየከዳኝ፤
የሽብር ማዕበል ጐርፍ ሲጦልፈኝ፤
አገር ህልሜን ይፍታ፤ቅዥት አይሁነኝ፤
በአካል በመንፈስም በስሜ ጥሩኝ፤
**የለውጥ ሃዋርያ እኔ እስክንድር ነኝ።**

yegonchaw@yahoo.co.uk

Ethiopia Will Prevail!

EthioLion.Com